ሰነዶች በማቅረብ ስም እንዲያዛውርላቸው የሚመለከተውን የአስተዳደር መ/ቤት ከሚጠይቁ በቀር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም፡፡ በመሆኑም 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አላገኘውም፡፡

**ው ሣ ኔ**

1/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 11201 ጥቅምት 9 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24848 ጥቅምት 26 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

2/ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ሰኔ 16ቀን 1984 ዓ.ም. ያደረጉት ስጦታ ውል ፈራሽ ሊሆን አይገባም፡፡

3/ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችና በ3ኛ ተጠሪ መሀከል በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል በሚገኘው በ220 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ ያረፈው ቁጥር 272 በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው፡፡

4/ 4ኛ ተጠሪ በተራ ቁ. 3 ላይ የተገለፀውን ቤት ስመ ንብረት እንዲያዛውር የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት ስለሌለው ተቀባይነት የለውም፡፡

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ 23921

ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
መስፍን እቁበዮናስ
ብርሃኑ አመነው

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግሥቱ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- 10 አለቃ ታደሰ ወርቁ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ፍርድ ቤት ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ለተጠሪው በጥር 1989 ዓ.ም. ያደረግሁት የስጦታ ውል በማታለል የተደረገና ተጠሪውም ሊጦረኝ ሲገባ ስለማይጦረኝ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት በማጣቱና ይግባኝ አቅርባም ይግባኙ በመሠረዙ ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ያደረገው በጉድለት ምክንያት ውል እንዲሠረዝ የሚቀርብ ጥያቄ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል፤ በማለትና ተጠሪ አመልካችን የመጦር ግዴታ በውሉ አልተሰጠውም በማለት ነው፡፡

እኛም የስጦታ ውሉ ሊፈርስ የሚገባው መሆን ያለመሆኑን አይፈርስም ከተባለስ ተጠሪው ስጦታ ሰጪዋን አመልካችን ሊጦር ይገባል ወይንስ አይገባም የሚሉትን ነጥቦች መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለተ አመልካች ለተጠሪው የስጦታ ውል ያደረገችው ጥር 27 ቀን 1989 ዓ.ም ሲሆን ይህ የስጦታ ውል እንዲፈርስ ክስ የመሠረተችው ደግሞ በግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም ነው፡፡ የፍ/ሕ/ቁ 2441/1/ ሥጦታ እንዲቀነስ ወይም እንዲሻር የሚቀርብ ጥያቄ ሥጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ እስከ ሁለት ዓመት ካልቀረበ በቀር ዋጋ የሌለው እንደሆነ